# ከስራ የመውጣት ካሳ ለማግኘት እንዴት ማመልከቻ እንደሚያስገቡ

**የዲስትሪክቱ ሰራተኞች ከስራ የመውጣት ካሳ ለማግኘት በ www.dcnetworks.org በመግባት ሊያመለክቱ ይችላሉ።**

ማመልከቻዎን ለመጀመር የሚከተሉትን ዝግጁ ማድረግ አለቦት፣

- የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥሮን
- በመጨረሻዎቹ 30 ቀናት የነበሮት የአሰሪዎ ስም፣ አድራሻ ፣የስልክ ቁጥርና የተቀጠሩበት ዕለት
- የአሜሪካ ዜጋ ካልሆኑ፣ የውጭ ዜጋ ምዝገባ ቁጥሮ
- በውትድርናው ዓለም ከነበሩ የ DD214 መለያዎን
- የመንግስት ሰራተኛ ከነበሩ የስታንዳርድ ፎርም 8 (Standard Form 8) ወይም የስታንዳርድ ፎርም 50 (Standard Form 50)
- የሚከፈሉት የመልቀቅያ ክፍያ መረጃ( ይህ የሚሰራው የሚከፈሉት የመልቀቅያ ክፍያ ካለ ወይም ወደፊት የሚያገኙ ከሆነ ብቻ ነው)
- የጡረታ መረጃ( ጡረታ የሚቀበሉ ከሆነ)
- **በ ህዝብ ጤንነት ላይ የመጣውን አደጋ በሚመልከት ማረጋገጫ ዶኩመንት( በተለይ በኮሮናቫይረስ-(COVID-19) ምክንያት ከሆነ ከሰራ የወጡት)። ማረጋገጫዎቹ የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፣**
  - ❖ ከሰው ለመገለል ያስፈልገኛል ተብሎ በቀረበ ጥያቄ መሰረት ወይም በግዳጅ እንዲገለሉ መደረጎን የሚያመልከት የሓኪም ወረቀት
  - ❖ ከሓኪሞ ወይም ከሕክምና መዝገብ ጽሕፈት ቤት ወደስራ ራሶን ማግለል እንዳለቦት ሃሳብ የሚያቀርብ/ የሚጠይቅ ወረቀት
  - ❖ በጤን ጥበቃ ክፍል የወጡት ራስን የመገልል ምልክቶች እኔንም ይመለከታሉ ብለው ራስዎን በራሶ ሲያገሉ

## የብቁነት ማሳያዎች

የስራ መውጣት ካሳ ገንዘብ ከመንግስት ለመቀበል ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ማሟላት ይገባል:

1. ከስራ የወጡት በእርስዎ ጥፋት ካልሆነ
2. መስራት የሚችሉ ከሆነ
3. ለመስራት ዝግጁ ከሆኑ ( በኮሮናቫይሩስ (COVID-19)ምክንያት ከቤት እንዳይወጡ ካልታገዱ በስተቀረ
4. ስራ ለማግኘት መሯሯጥ ( ከስራ የወጡበት ምክንያት በኮሮናቫይሩስ (COVID-19))ካልሆነ በስተቀረ)

## በኦንላይን ማመልከቻ ማስገባት

1. በኦንላይን ወደ www.dcnetworks.org ይግቡና "ክሌም ኦን ኢምፕሎይመንት ቤነፊት" (Claim Unemployment Benefits) የሚለውን ይጫኑ።
2. በስራ መውጣት የኢንሹራንስ ጠቀሜታ አገልግሎት ማእከል፣ የአመልካቾች ገጽ በሚለው ላይ፣ ፋይል ፎር ቤነፊትስ( File for Benefits) የሚለውን ይጫኑ።
3. ወደ ገጹ ወደታች በኩል ይሂዱና "ፋይል ዮር ክሌም ኦን ላይን"(File Your Claim On-Line) የሚለው ላይ ይጫኑ
4. የማመልከቻ ሂደቱን በሙሉ ለማጠናቀቅ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን ይስጡ።

## ደንበኞችን የሚመራ ማእከል

አመልካቾች በኦንላይን www.dcnetworks.org ውስጥ በመግባት ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ እናበረታታለን። ይህንን ለማድረግ ግን ችግር ከገጠሞት ከ ዲ-ኦ-ኢ-ኤስ ደንበኞችን የሚመራ ለመገናኘት በስልክ ቁጥር 202-724-7000 ይደውሉ።